# የአብሮ መኖራችን ዋስትና

አብዱልጀሊል ከባሌ ሮቤ firanboni2000000@gmail.com

አንዳንድ ግለሰቦችና የፖለቲካ ፓርቲዎች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠልን የሚቃወሙት የአንቀጽ 39ን መርህ መሠረታዊ ይዘትና ሕገ-መንግሥቱ የሚያስቀምጣቸውን ነጥቦች በተሟላ መልኩ ካለመገንዘብ የመጣ መሆኑን ከገለጻቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ አባባል ሕገ-መንግሥቱን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አያይዞ ለመገንዘብ የሚቸገሩ ሰዎች እንዳሉ የሚያመለክት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሕገ-መንግሥታችን የሚያስቀምጠውን መሠረታዊ አቅጣጫ በይበልጥ ለመረዳት የጉዳዩን ታሪካዊ አመጣጥ በአጭሩ መቃኘት ይበጃል፡፡

አገራችን የበርካታ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አገር ነች፡፡ ሆኖም በብሔር፣ ብሄረሰቦች መካከል የነበረው አስተዳደራዊ ግንኙነት በየጊዜው መልኩን እየቀያየረ የመጣ ቢሆንም በመሠረታዊ ይዘቱ ኢ-ዴሞክራሲያዊ  የነበረ ነው፡፡ የአገሪቱ መሪዎች ይህንን ብዙህነት ማስተናገድ አቅቷቸው አንዴ ስትወድቅ አንዴ ስትነሳ የኖረች አገር ናት ፡፡

ለምሳሌ የአካባቢው ብሔር፣ ብሔረሰብ እያለ ከሌላ ቦታ አምጥተው ሕዝቡ የማያውቀውን በእንደራሴነት እንዲተዳደር ይደረግ እንደነበረ ታሪክ የሚረሳው አይደለም ፡፡ ነገሩ ቋንቋህን ተው በእኛ ቋንቋ ተናገር፣ ካልቻልክ ዝም ብለህ ተቀመጥ ፣ ከፖለቲካው ከኢኮኖሚና ከማህበራዊ ጉዳዮች ባይተዋር ሆነህ መኖር አለብህ ዓይነት ዘይቤ ነበረው፡፡ ተሹመው የሚላኩ ባለስልጣናትም የህዝቡን ቋንቋ፣ ባህል ወዘተ የሚያከብሩ ሳይሆኑ የራሳቸውን ባህልና ሃይማኖት በሌሎች ላይ በኃይል የሚጭኑ ነበሩ፡፡ ልማትንም በተመለከተ የሥርዓቱን አቀንቃኞች ጥቅም በማስጠበቅ ላይ የተመሠረተ እንጅ ለአካባቢው ህዝብ ምንም የሚፈይደው ነገር አልነበረም፡፡

እነዚህ ሕዝቦች አንድነታቸውና ወንድማማችነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የየራሳቸው ቋንቋ ባህል፣ ታሪክ ወዘተ የሚታወቁበትና የሚከበሩበት ዕድል ተነፍጓቸው ነበር የቆየው፡፡ እንደትላንቱ ዛሬም አንዳንድ ግለሰቦችና ፓርቲዎች ይህንን የቋንቋ፣ የባህል፣ የሃይማኖት ወዘተ ልዩነት ያላቸው ሕዝቦች መኖራቸው የሕዝባዊ አንድነታችን ጥንካሬ ምንጭ ሳይሆን የአንድነታችን ፀር አድርገው ሲወስዱ ይስተዋላል፡፡ ይህ ደግሞ በአገር አንድነት

ስም ብሄራዊ ጭቆና ዳግም ይመለስ እያሉ ነው እንጂ ለብዙህነት መፍትሄ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ እንዳልሆነ ለማንም ግልጽ ነው፡፡

ስለዚህ ይህንን ልዩነት በዴሞክራሲያዊ መንገድ አቻችሎ ከመሄድ ይልቅ ሕዝቦች ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ ሃይማኖታቸውን ወዘተ. እንዳያሳድጉ ለማፈንና በአስተዳደራዊ መንገድ እነዚህ እሴቶችን እንዲያጡ ለማድረግ እየሞከሩ ነው፡፡

ጥንትም በአስተዳደራዊ መንገድ አንድ ቋንቋ፣ ባህልና ኃይማኖት ወዘተ በሃይል እንዲኖረን ነበረ የተደረገው፡፡ ዛሬም በዚሁ መንገድ እንጓዝ የሚሉ የሞተው ሥርዓት የታሪክ ባለአደራዎች አሉ፡፡ አገሪቱ ከ100 ዓመት በላይ እነሱ በሚሉት አንድነት ታጥራ ብትቆይም የልማት፣ የዴሞክራሲ እና መልካም አስተዳደር ምድረ-በዳ ሆና የቆየችና በውስብስብ ችግር እንድትተበተብ ከመደረግ ያለፈ ለልማት ያበረከተው አንዳችም ነገር አልነበረም። እነርሱ የሚሉት አንድነት የሕዝቦችን ባህል፣ ቋንቋ ወዘተ ልዩነት አስታርቆ አገርን ማሳደግና መለወጥ ያልቻለ መሆኑን በተግባር ፈትሸን ያለፍነው ሥርዓት ነው፡፡ ትርፉ ጦርነት፣ ረሀብ፣ ድንቁርና የሰብዓዊ መብት ጥሰትን ያስከተለ ህዝቦችን ለስደት እና እንግልት የዳረገ አልነበረምን ;

የብሔር ብሔራሰብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ጥያቄ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ብቅ ያለው ሕገ-መንግሥታችን ሲጸድቅ አይደለም፡፡ በንጉሱ እና በደርግ አገዛዝ ዘመን እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ በተለይ በደርግ መንግሥት ውድቀት ዋዜማ ላይ የብሔረሰብ ጥያቄን አንግበው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ቢያንስ 17 ታጣቂ ድርጅቶች ነበሩ፡፡ ኢትዮጵያን የመበታተን አደጋ ገጠማት የተባለበት ያ አስከፊ ወቅት አልፎ የሽግግሩ ጊዜ ቻርተር ከዚያም ህገ መንግስቱ ከፀደቀ በኋላ ሃገራችን በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የፀና አንድነት እንዲኖራት ሆናለች።

እስቲ ሕገ-መንግሥታችን የሚለውን እንይ፡- አንዳንዶች እንደሚሰብኩት ሳይሆን ሕዝብ በራሱ ቋንቋ መጠቀም እንዲችልና በዴሞክራሲ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ያስቻለ ሕገ-መንግሥት ነው፡፡ ሕዝቡ በየክልሉ በየቋንቋው እየተጠቀመ የአካባቢውን ጉዳዮች መወሰን ካልቻለ ቀጥተኛ የፖለቲካ ስልጣን ተሳትፎ ሊኖረው አይችልም፡፡ በሥማ በለው የሚተዳደር ህብረተሰብ በልማት ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊያደርግ አይችልም፡፡ ሕዝቦች በቋንቋችን እንናገር፣ ባህላችን ይከበር፣ ታሪካችን ይህ ነው ብለው መጻፍ መናገርና ሐሣባቸውን መግለፅ ካልቻሉ መብታቸው ተከበረ ሊባል አይችልም፡፡ ቋንቋ፣ ባህል

ወዘተ የማንነት ዋንኛ መገለጫዎች ናቸውና። ለዚህም ነው ህገ መንግስታችን ለብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት መከበር ቅድሚያ የሰጠው።

ህገ መንግስቱ ዘመናዊ ከመሆኑ አንፃር በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ጠባብና ትምክህተኛ አመለካከቶች እንኳን በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ እንዳይቀርቡ የሚያግድ አይደለም ፡፡ እነዚህን በሕግ ማገድ ማለት ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ሁሉ ማገድን ስለሚያስከትል ነው ፡፡ የተሳሳቱ ሃሳቦችም ቢሆኑ የሌሎችን መብት ሳይደፍሩ፣ ጦርነት ሳይቀሰቅሱ እንዲቀርቡ መፍቀድ፣ እነዚህን የተሳሳቱ አመለካከቶች በተስተካከሉ አመለካከቶች በሰላማዊ መንገድ ማጋለጥ ማፍረስና በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው የማድረግ ስልትን ነው የሚከተለው እንጂ የሀሳብን የመግለጽ መብትን የሚያፍን አይደለም፡፡ ማንም ሃሳቡን በሰላማዊ መንገድ መግለፅ እስከቻለ ድረስ ገደብ ሊደረግበት እንደማይችል ህገ መንግስቱ በግልፅ ያስቀምጣል።

የብሔር ቅራኔ እጅግ የሰላ ደረጃ ላይ ደርሶ በነበረበት በ1980ዎቹ አጋማሽ ላይ አገራችን በርካታ ጠባብና ትምክህተኛ አመለካከት ያላቸው ድርጅቶችና ቡድኖች ሃገሪቱን ለማመስ ሲጥሩ በነበረበት ጊዜ እንኳን ግለሰቦችና ቡድኖች ሃሳባቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲገልፁ እንጂ እገዳ የተጣለበት ጊዜ የለም።፡፡ እነዚህ ወገኖች ሃሳባቸውን በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ መግለፅ ካልቻሉ የዜጎቹ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩበት ሥርዓት ሊታሰብ አይችልም፡፡ ይልቁንም ሃሳባቸውን በነጻነትና ዴሞክራሲያዊ አኳኋን እንዲያቀርቡ ፈቅዶ በተመሳሳይ ዲሞክራሲያዊ አኳኋን ሃሳባቸው በሕብረተሰቡ ተቀባይነት እንዳይኖረው ማድረግና ተገቢ ጥያቄዎችን በመፍታት አስተሳሰባቸውን ከምንጩ ለማድረቅ መታገል ብቸኛው ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ነው፡፡

ስለዚህ ሕገ-መንግሥታችን በአንድ በኩል የብሔር ብሔረሰቦችን የማንነት ጥያቄዎች በመመለስ ለአንድነታችን ፀር የሆኑ አስተሳሰቦችን በዴሞክራሲያዊና አስተማማኝ አኳኋን ለማምከን የሚያስችል በር ሲከፍት፣ በሌላ በኩል ደግሞ አንዱ የሌላውን መብት ደፍሮ ሰላምን ሲያደፈርስ በህግ ተጠያቂ እንዲሆን አድርጓል። ይህም የህግ የበላይነት በሃገሪቱ እንዲሰፍን ትልቅ ድርሻ አበርክቷል። በዚህ አኳኋን የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሊከበሩ የሚችሉበትን ሁኔታ አመቻችቷል፡፡ ብሔር ብሔረሰቦች ሃሳባቸውን የመግለፅ መብታቸው ባልተከበረበት ሁኔታ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማስከበር

ፈፅሞ አይቻልም፡፡ እነዚህ መሰረታዊ መብቶች ከታፈኑ ሕገ-መንግሥቱ የመገንጠል መብትን ቢፈቅድም ባይፈቅድም ሕዝቡ ወደ ግጭት ገብቶ መበታተኑ አይቀሬ ነው፡፡

ይልቁንም የብሔሮችን መሰረታዊ መብቶች  በሕግ አረጋግጦ ፣ የጠባቦችና ትምክህተኞችን አስተሳሰብ ከምንጩ ለማድረቅ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነው። ሕገ-መንግሥታችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል መከበር አለበት የሚለው በሕዝቦች መካከል ቀጣይ ልዩነትና ቁርሾ እንዲኖር ለማድረግ አይደለም፡፡  ይልቁንመ በሕዝቦች መካከል በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለመፍጠር ያለመ ነው፡፡ አንድነታችን ብሔረሰባዊ እሴቶችን በአስተዳደራዊ መንገድ በማጥፋት ሊገነባ እንደማይችል በተግባር የተረጋገጠ ሃቅ በመሆኑ ይህን አስወግዶ የጠንካራ ሕዝባዊ አንድነት መሠረቶችን ለመጣልና ለማጠናከር ነው፡፡

በሕገ-መንግሥቱ መግቢያ ሦስተኛ አንቀጽ ላይ #የየራሳችን ብሔረሰባዊ እሴቶች ያሉን ሕዝቦች ብንሆንም ባለፈው ታሪካችን ሂደት ለአንድነታችን መሰረት የሚሆኑ የጋራ ጥቅሞችና አመለካከቶች አፍርተናል$ የሚል ሰፍሯል፡፡ እነዚህ ታሪካዊ እሴቶች የፖለቲካዊ አንድነታችን መሠረቶች መሆናቸውንም ያስረዳል፡፡ በታሪካችን የተዛቡ ግንኙነቶችንም በማስተካከል አንድ የፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማሕበረሰብ፣ አንድ የተከበረ አገር ለመፍጠር በነጻ ፍላጎታቸው መርጠው የወሰኑ መሆኑን በህገ-መንግስቱ አንቀፅ አራት ላይ  በግልጽ ሰፍሯል፡፡ ብሔረሰባዊ እሴቶች የኢትዮጵያዊነት እሴቶች መሠረት እንጂ የኢትዮጵያዊነት እሴቶችን የሚፃረሩ አይደሉም፡፡ ተጻራሪ እንዳይሆኑም ማድረግ የሚቻለው በዴሞክራሲያዊ ትግል ብቻ ነው፡፡

ይሄው ሕገ-መንግሥት በመግቢያው ላይ ጠንካራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አገራዊ አንድነት መፈጠር የሚቻልበትን አቅጣጫ ሲያመላክት በሌላ በኩል ደግሞ በአንቀጽ 39 ላይ በማያሻማ መልኩ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል አስቀምጦ ተግባራዊ የሚሆንበትንም መንገድ በዝርዝር ያስረዳል፡፡ ይህንን መሰረታዊ ሐሳብ ለመገንዘብ ሕገ-መንግሥቱ ለዚህ መብት እውቅና ባይሰጥ ምን ይፈጠር ነበረ ከሚለው አቅጣጫ መመልከት ይሻል፡፡ ሕዝቡ በአንድነት እንዲኖር የተደረጉ ዲሞክራሲያዊ ጥረቶች ካልተሳኩ የሚኖረው አማራጭ አንድ ብቻ ነው፡፡ አብሮ መኖር ያልፈለገን ሕዝብ በጉልበት፣ በኃይል ለማስቀረት መሞከር ወደ ጦርነት ማምራት ይሆናል፡፡ አንድነትን በጉልበት ማስጠበቅ አንድ ቀን መክሸፉ ስለማይቀር እስከዚያው ድረስ ግን

አገሪቷን በአስከፊ ጦርነት ውስጥ መዝፈቅና የሰላም ፣ የልማትና የዴሞክራሲ አላማዎችንም ለከፍተኛ አደጋ ማጋለጥ ነው።

ለመገንጠል መብት እውቅና የሰጠ ሕገ-መንግሥት ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ያከበረ ስለሆነ የህዝቦችን መብት በጉልበት አስሮ የማኖሩ ሙከራ የሚያስከትለውን ጥፋት ያስቀራል፡፡ ለመገንጠል መብት እውቅና ያልሰጠ ሕገ-መንግሥት የመገንጠል ጥያቄ ሲነሳ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሕዝቡን ማሳመን ካልቻለ ጥያቄውን መፍታት የሚያስችል ምንም ቀዳዳ ስለሌለው ወደ አስከፊ ጦርነት ማምራቱ አይቀሬ ይሆናል፡፡

ሕገ-መንግሥቱ አንድነታችንን ማረጋገጥ የሚያስችለው ብቸኛ መንገድ ሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ መንገድ አንድነታችንን ለማረጋገጥ መሞከር የማይሳካ ነገር ብቻ ሳይሆን አገራችንን ለከፋ አደጋ ያጋልጣል የሚል መነሻ አለው፡፡ ስለዚህ ይህ መብት በሕገ-መንግሥቱ ላይ ሠፈረም አልሰፈረም ብሔር ብሔረሰቦች ጭቆና የሚደረግባቸው ከሆነ ሀገር ወደ መበታተን ማምራ~ እንደማይቀር በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የተከሰተውን ማስታወስ ይጠቅማል፡፡

ሕገ-መንግሥታችን የመገንጠል መብትን በማያሻማ መልኩ እንዲከበር መፍቀዱ መገነጣጠልን ማራመዱ ወይም መስበኩ ሳይሆን ብቸኛውን የሰላምና የአንድነት አማራጭ መምረጡ ነው፡፡ እንደውም ይህ አንቀጽ አንድ አስከፊ ሥርዓት በአገራችን ዳግም ቢከሰት ለሕዝቦች መብት መከበር ዋስትና ነው፡፡ መንግሥትም የሕዝቦች መብት ያለገደብ እንዲያከብር፣ ልማት፣ ዴሞክራሲና ሰላም እንዲሰፍን ፣ የሁሉንም ፍላጎትና የሕዝብ የልማት ተጠቃሚነት እንዲሟላ ለማድረግ የሚገደድበት ይሆናል፡፡ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች እንዳይከፋቸው የሚያደርግ እና የመብት አፈናን የሚያስቀር በፍላጎት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲጠናከር የሚረዳ አንቀጽ ነው፡፡ አንድ ሕዝብ ጥያቄው በሰላማዊና ዴሞክራሲያ መንገድ ከተሟሉለት ከሌላው ጋር አብሮ በመኖር ተጠቃሚ ይሆናል እንጂ አይጎዳም። የሕዝቦቻችንን ፈጣን ልማትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን አንድነት ማረጋገጥ አስፈላጊ እንደሆነ የመንግሥት ጽኑ እምነት መሆኑን መንግሥት በተለያዩ ጊዜያት ከሰጣቸው መግለጫዎች መረዳት ይቻላል፡፡

እንግዲህ አንቀፅ 39ን መቃወም ማለት የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ወደ ጎን ትቶ ዛሬም እንደትላንቱ የሕዝቦች የእኩልነት መብትን አለመቀበል ማለት ነው፡፡ ይህ አንቀፅ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን ያስተሳሰረ እንጂ አንዳንድ የቀድሞ ስርአት ናፋቂዎች እንደሚያቀነቅኑት ሃገርን የሚበትን እንዳልሆነ ካለፉት ሁለት አስርት አመታት መረዳት ይቻላል።